IslamHouse.com



Amharic
አማርኛ
أمهري

# أحكام صوم رمضان

# የፆመኛ ሙስሊም መመሪያ


በሸኽ
ሙሐመድ ቢን ሷሊህ አል-ኡሰይሚን

ትርጉም
ኡስታዝ አህመድ የሱፍ

አርማት
ሸኽ ጀማል ሸኽ ሙሐመድ

Amharic
አማርኛ
أمهري

# أحكام صوم رمضان


تأليف

الشيخ صالح العثيمين

الترجمة

احمد يوسف

مراجعة

الداعية جمال محمد أحمد

مركز أصول
Osoul Center
www.osoulcenter.com

أُعد هذا الكتاب وصمِّم من قبل مركز أصول، وجميع الصور المستخدمة في التصميم يملك المركز حقوقها، وإن مركز أصول يتيح لكل مسلم طباعة الكتاب ونشره بأي وسيلة، بشرط الالتزام بالإشارة إلى المصدر، وعدم التغيير في النص، وفي حالة الطباعة يوصي المركز بالالتزام بمعاييره في جودة الطباعة.

+966 504 442 532
+966 11 445 4900
+966 11 497 0126
P.O.BOX 29465 Riyadh 11457
osoul@rabwah.com
www.osoulcenter.com

بسم الله الرحمن الرحيم

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ
እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው

الحمد لله رب العالمين الصلاة والسلام على رسول الله وعلى آله وصحبه

የሰው ልጅ ያለ መመሪያና ደንብ ልጓም እንደሌለው ፈረስ በመሆኑ በየትኛውም የህይወት ዘርፍ የሰው ልጅ መመሪያ ያስፈልገዋል።

ሆኖም ፆመኛ ሙስሊም እንደሌሎቹ የእምነቱ ስርአት ሊከተላቸውና ሊተገበራቸው የሚገቡ መመሪያና ደንቦች እንደሚከተለው ተብራርተዋል።

የፆመኛ ሙስሊም መመሪያ

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

በሸኽ ሙሐመድ ቢን ሷልህ አል-ኡሰይሚን

ትርጉም በአህመድ የሱፍ

ምስጋና ለአለማት ጌታ ለአሏህ ይገባው። የአሏህ ሰላምና እዝነት የነብያቶች መደምደሚያ በሆኑት በነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ)፣ በቤተሰቦቻቸውና በሶሃቦቻቸው ላይ ይሁን።

ማንኛውም ሙስሊም ሊያውቃቸው የሚገቡ ጠቃሚ የፆም ህግጋቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

# ፆም ምንድነው?

ሲያም(ፆም)_ ከንጋት ጀምሮ ፀሐይ እስከምትጠልቅበት ጊዜ ድረስ ከምግብ ፣ ከመጠጥ እና ከግብረስጋ ግኑኘነት እንዲሁም ከሃራም ነገሮች ሁሉ በመቆጠብ አሏህን መገዛት ነው።

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ﴾ [البقرة: ١٨٣]

እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።

﴿ أَيَّامٗا مَّعۡدُودَٰتٖۚ فَمَن كَانَ مِنكُم مَّرِيضًا أَوۡ عَلَىٰ سَفَرٖ فَعِدَّةٞ مِّنۡ أَيَّامٍ أُخَرَۚ وَعَلَى ٱلَّذِينَ يُطِيقُونَهُۥ فِدۡيَةٞ طَعَامُ مِسۡكِينٖۖ فَمَن تَطَوَّعَ خَيۡرٗا فَهُوَ خَيۡرٞ لَّهُۥۚ وَأَن تَصُومُواْ خَيۡرٞ لَّكُمۡ إِن كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ﴾ [البقرة: ١٨٤]

የተቆጠሩን ቀኖች (ጹሙ)። ከእናንተም ውሰጥ በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የኾነ ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን መጾም አለበት። በእነዚያም ጾምን በማይችሉት ላይ ቤዛ ድኻን ማብላት አለባቸው። (ቤዛን በመጨመር) መልካምንም ሥራ የፈቀደ ሰው እርሱ (ፈቅዶ

መጨመሩ) ለርሱ በላጭ ነው፡፡ መጾማችሁም ለናንተ የበለጠ ነው፤ የምታውቁ ብትኾኑ (ትመርጡታላችሁ)፡፡

﴿شَهْرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِىٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلْقُرْءَانُ هُدًى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَٰتٍ مِّنَ ٱلْهُدَىٰ وَٱلْفُرْقَانِ ۚ فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهْرَ فَلْيَصُمْهُ ۖ وَمَن كَانَ مَرِيضًا أَوْ عَلَىٰ سَفَرٍ فَعِدَّةٌ مِّنْ أَيَّامٍ أُخَرَ ۗ يُرِيدُ ٱللَّهُ بِكُمُ ٱلْيُسْرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ ٱلْعُسْرَ وَلِتُكْمِلُوا۟ ٱلْعِدَّةَ وَلِتُكَبِّرُوا۟ ٱللَّهَ عَلَىٰ مَا هَدَىٰكُمْ وَلَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ﴾ [البقرة: ١٨٥]

(እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲኾን ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፡፡ ከእናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው፡፡ በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የኾነም ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መጾም አለበት፡፡ አላህ በእናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በእናንተም ችግሩን አይሻም፡፡ ቁጥሮችንም ልትሞሉ አላህንም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህን ደነገግንላችሁ)፡፡



# የፆም ጥቅም

የረመዷን ፆም አንዱ የኢስላም ምሶሶ ነው። ይህን በተመለከተ የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) ኢስላም የተመሰረተው(የተገነባው) በአምስት ምሶሶዎች ላይ ነው ብለዋል። እነሱም፦

01 ከአሏህ ውጭ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) የአሏህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር።

02 ሶላት መስገድ

03 ዘካ መክፈል

04 ሐጅ ማድረግና

05 በረመዷን ወር መፆም ናቸው።

# የፆም ህግጋቶች

01 ፆም ጎልማሳ በሆነ ፣ ጤናማ አዕምሮ ባለውና መፆም በሚችል ማንኛውም ሙስሊም ወንድም ሆነ ሴት ላይ ግዴታ ነው።

02 አማኝ ያልሆነ ሰው አይፆምም፤ ቢፆምም ተቀባይነት የለውም። ምናልባት አሏህ ቀጥተኛውን መንገድ መርቶት ኢስላምን ቢቀበል ያለፉትን የፆም ቀናት ማካካስ አይጠበቅበትም።

03 ፆም ለህፃናት ግዴታ አይደለም። ነገርግን ይለምዱት ዘንድ እንዲፆሙ መበረታታት ይኖርባቸዋል።

04 አዕምሮው የተዛባ ሰው መፆምም ሆነ ሰዎችን በመመገብ ማካካስ አይገደድም።

05 ለዘለቄታው መፆም የማይችሉ ሰዎች ለምሳሌ በጣም ያረጁና ስር በሰደደ ህመም እየተሰቃዩ ምንም የማገገም ተስፋ የሌላቸው ሰዎች በመፆም ፈንታ ድሆችን መመገብ ይጠበቅባቸዋል።

06 ታሞ የማገገም ተስፋ የሌለው ሰው ፆሙ አስቸጋሪ ከሆነበት ፆሙን ሊያፈርስ ይችላል። ሆኖም ግን ካገገመ ብኋላ ያለፈውን ቀን ማካካስ ይኖርበታል።

07 ነፍሰጡር ሴቶችና ጡት የሚያጠቡ እናቶች በረመዷን ወቅት

መፆም አስቸጋሪ ከሆነባቸው ወይም ልጄ ይጎዳብኛል ብለው ከፈሩ ፆማቸውን መፍታት ይፈቀድላቸዋል። ብኋላ ላይ ግን ያለፉቸውን ቀናት ማካካስ ይኖርባቸዋል።

08 የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ላይ የሆኑ ሴቶች በዚህ ወቅት መፆም አይፈቀድላቸውም። ነገርግን ብኋላ ላይ ያለፉቸውን ቀናት ማካካስ ይገደዳሉ።

09 ምንገደኛ ሰው መፆም ወይም ደግሞ አለመፆም የሚችል ሲሆን ካልፆመ ብኋላ ላይ ያለፉትን ቀናት ማካካስ ይኖርበታል።




# ፆምን የሚያበላሹ ነገሮች

ፆመኛ ሁነን ሳናስበው ዘንግተን(ረስተን) ብንበላ ወይም ብንጠጣ ወይም ደግሞ ተገደን እንድንበላና እንድንጠጣ ብንደረግ ፆማችን አይበላሽም። ሃያሉ አሏህ በቁዱስ ቁርአን እንዲህ ይላል፡-

ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንስት አትያዘን(አትቅጣን) (በሉ)። {አል-ቁርአን 2:286}

ልቡ በኢማን ረግታ ይህን እንዲያደርግ ከተገደደ ሰው በቀር {አል-ቁርአን 16:106}

ልባችሁ ሆንብሎ ባሰበው እንጅ ሳታውቁ በሰራችሁት ስህተት ሃጢያት የለባችሁም። {አል-ቁርአን 33:5}

ስለዚህ ሳናውቅ ረስተን ብንበላ ወይም ብንጠጣ ፆማችን አይበላሽም። እንዲሁም ፀሐይዋ በመጥለቋ ምሽቱ ጀምሯል ብለን በማሰብ ብንበላና ብንጠጣ ወይም ደግሞ ንጋቱ ገና እንዳልጀመረ አስበን ብንበላ ብንጠጣ ፆማችን አይበላሽም። በተመሳሳይ መልኩ እየፆምን እንዳለ የዘር ፈሳሻችን ሳናስበው ቢፈስ ፆማችን አይበላሽም።

ፆም የሚያበላሹ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ፆም በሚከተሉት ስምንት ነገሮች ይበላሻል።

01 ግብረ ስጋግኑኝነት ማድረግ: ፆም ግዴታ የሆነብን ሰዎች

በረመዷን ቀን ላይ ወሲብ ከፈፀምን ይህን ቀን ማካካስና መቶበት ይኖርብናል። ያለፈንን ቀን ለማካካስ አንድ ባርያ ነፃ ማውጣት ይጠበቅብናል። ይህን ማድረግ ካልቻልን ሁለት ወር በተከታታይ መፆም ይኖርብናል። ይህንንም ማድረግ ካልቻልን ስልሳ ድሆችን መመገብ ይኖርብናል።

02 ሆንብሎ የዘር ፈሳሽን ማፍሰስ: ለምሳሌ ከራስ ብልት ጋር በእጅ በመጫወት ፣ በመሳምና በማቀፍ

03 ሆንብሎ መብላት መጠጣት

04 የምግብ መርፌ መወጋት ፆም ያበላሻል። ምክኒያቱም ከመብላትና ከመጠጣት ጋር ተመሳሳይ ነውና።

05 ደም መለገስ (መስጠት): ፆመኛ ሰው በሰውነቱ ውስጥ ብዙ ደም ፈሶት እንዲያገግም ደም ቢለገሰው ፆሙ ይበላሻል።

06 የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም

07 የዋግምት ደም መፍሰስ: ደም በራሱ ጊዜ ከአካል ከፈሰሰ ፆም አያበላሽም። ለምሳሌ የነስር ደም ወይም ደግሞ ጥርስ ከተነቀለ ብኋላ የሚፈስ ደም

08 ጣታችነን ወደ ጉሮሯችን በማስገባት ሆንብለን እንዲያስታወከን ብናደርግ ፆማችን ይበላሻል። ሳናስበው በድንገት ቢያስታውከን ግን ፆማችን አይበላሽም።




# ጠቃሚ መረጃዎች

01 የፆም ንያን ጀናባ በሆንበት ጊዜ ቢሆንኳ መነየት የምንችል ሲሆን ከንጋት ብኋላ መታጠብ እንችላለን።

02 የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ምሽት ላይ ያቆመላት ሴት ቀጣዩን ቀን ለመፆም መነየት ይኖርባታል። ጉሱል (ሙሉ ትጥበት) እስከ ንጋት ድረስ ማዘግየት ትችላለች። ነገርግን ሙሉ ትጥበቷን ከፈጅር ሶላት በፊት መፈፀም ይኖርባታል።

03 ፆመኛ ሰው ጥርሱን መንቀል ፣ ቁስሉን ወይም ጉዳት የደረሰበትን የአካል ክፍል ማከም ፣ የአይን ጠብታ መጠቀም ይችላል። ሆኖም የአይን ጠብታው ጣዕም በጉሮሮው ቢወርድ ፆሙ አይበላሽም።

04 ፆመኛ ሰው ሲዋክ ወይም የጥርስ ብሩሽ በመጠቀም ጥርሱን ማፅዳት ይችላል። ቀኑን ሙሉ ወይም ከሶላት በፊት ጥርስን በሲዋክ መፋቁ ሱና ነው።

05 ፆመኛ ሰው በሞቃት የአየር ንብረት ወይም በውሃ ጥም ቢቃጠል ይህን የሚያቀልለትን ነገር ማድረግ የሚችል ሲሆን ሰውነቱን ለማቀዝቀዝ ውሃ ወይም የአየር ማቀዝቀዣ መሳሪያ መጠቀም ይፈቀድለታል።

06 በጭንቀት ወይም በሌላ ችግር ምክኒያት የመተንፈስ ችግር

ያጋጠመው ፆመኛ የአተነፋፈስ ስርአቱን ለማስተካከል አፉ ውስጥ የሆነ ነገር መርጨት ወይም መሳብ ይችላል።

07 አፍን መጉመጥመጥና አፍንጫን ወይም የደረቁ ከናፍሮችን በውሃ ማርጠብ ይፈቀዳል። ነገርግን እየፆመ በተጋነና መልኩ ብዙ ውሃ በጥልቀት ወደ አፍ ወይም ወደ አፍንጫ ማድረስ የተጠላ ነው።

08 ፀሐይ እንደጠለቀች ያለምንም ማዘግየት ወዲያውኑ ማፍጠር (ፆምን መፍታት) ሱና ነው።

09 በፆም ወቅት ብዙ መልካም ስራዎችን አብዝቶ መስራትና የተከለከሉ ነገሮችን ሁሉ መራቅ ሱና ነው።

10 ፆመኛ ሰው ዋጅብ (ግዴታ) የሆኑ ስራዎችን ሁሉ መስራት እና ከተከለከሉ ነገሮች ሁሉ መራቅ ይኖርበታል። ለምሳሌ የቀኑን አምት ስግደቶች በጀመአ መስገድ ይኖርበታል። ከተከለከሉ ነገሮች ደግሞ ለምሳሌ ሐሜት ፣ ውሸት መናገር ፣ ማታለል፣ አራጣ መብላት ወ.ዘ.ተ መከልከል ይኖርበታል። ይህን በተመልከተ የአሏህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) “ውሸት መናገርና መጥፎ ስራዎችን መስራት ያልተወ ሰው አሏህ ምግብና መጠጥ መተውን አይፈልግም” ብለዋል።





# ረመዷን: አሏህን የመፍራት ወር

ረመዷን ;; ወር ሙሉ ስሜቱንና መጥፎ ምኞቱን ተከትሎ ለኖረ ሰው ሁሉ ልጎም ፣ ለመልካም ሰሪዎች በረካ ሲሆን አዲስ የለውጥ ቤዛ ነው። ታዲያ ፆምን ፆም የሚያደርገው የምግብና የመጠጥ ተአቅቦ ብቻ ሳይሆን አሏህ የከለከላቸውን ነገሮች ሁሉ በመከልከል ያዘዛቸውን ነገሮች በመታዘዝ መልካም ነገሮችን መስራት ነው። ፆም.....በእናንተ ላይ ተደነገገ አሏህን ትፈሩ ዘንድ(2:183)።

ይህን ላደረገ ሰው ሲሳዩ በዱንያም በአሂራም ይሰፋል፤ እንከኖቹን አስወግዶ እራሱን በኢስላም ድስፕሊን በማነፅ የለውጥ ምሳሌ መሆን ይችላል። በረመዷን ወቅት ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከሌላው ጊዜ በበለጠ በኢባዳ ይተጉ ነበር።

ረመዷን: አሏህን የመፍራት ወር

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ
لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ﴾ [البقرة: ١٨٣]

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አሏህን ትፈሩ ዘንድ ፆም ከእናንተ በፊት በነበሩ ህዝቦች ላይ እንተደነገገው ሁሉ በእናንተም ላይ ተደነገገ። {አል-ቁርአን 2፡183}

ምስጋና ለሃያሉ አሏህ ይገባው። እናመሰግነዋለን ፣ እርዳታውን እንሻለን ፣ ምህተቱን እንለምናለን። ነፍሳችን ውስጥ ካለ ክፋትና ከወንጀል ስራዎቻችን ሁሉ በአሏህ እንጠበቃለን። አሏህ የመራውን ማንም አያጠምም፤ አሏህ ያጠመመውንም ማንም አይመራም። ከአሏህ ውጭ በሃቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ አለመኖሩንና ነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) የአሏህ ባርያና መልዕክተኛ መሆናቸውን እንመሰክራለን።

ረመዷን ከአምስቱ የኢስላም ምሶሶዎች አንዱ ሲሆን በሙስሊሞች የቀናት አቆጣጠር ደግሞ ዘጠንኛው ወር ነው። ሆኖም ይህን ወር አሏህ ቀን ላይ መፆምን ግዴታ ምሽት ላይ ደግሞ የተራዊህ ሶላትን ሱና አድርጎታል። የፆም ትርጉሙ መቆጠብ ሲሆን ከንጋት ጀምሮ ፀሐይ እስከምትጠልቅበት ጊዜ ድረስ ከመብላት ፣ ከመጠጣት ፣ ከግብረስጋ ግኑኝነት ፣ ከእንቶፈንቶ ወሬ ፣ ከማጨስ ፣ ከሃራም ነገሮች ሀሉ መቆጠብ ነው።

አል-ቡኻሪ ጥራዝ 3 መጽሐፍ 31 የሐ.ቁ 120

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ጀነት ውስጥ ረያን ተብሎ የሚጠራ በር አለ። በትንሳኤ ቀን ፆመኞች በእሱ በኩል የሚገቡ ሲሆን እነሱ እንጅ ከነሱ ውጭ ማንም አይገባም ብለዋል።

በረመዷን ወቅት ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከሌላው ወር በበለጠ በኢባዳ ይተጉ ነበር። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ቀኑን አሏህን በማስታወስ በዚክር ፣ በቁርአት ፣ በመማር ፣ ምክርና ትምህርት በመስጠት ያሳልፉ የነበረ ሲሆን ሌሊቱን ደግሞ ዱአ በማድረግ ፣ እራሳችነን ወደ አሏህ በማተናነስ በቂያመለይል ፣ እርዳታውን ፣ መመሪያውንና ድሉን በመሻት ያሳልፉ ነበር።

አል-ቡኻሪ ጥራዝ 3 መጽሐፍ 31 የሐ.ቁ 118



ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) አሏህ(ሱ.ወ.ተ) የሰው ልጅ የሚሰራው ሁሉም ስራ ለራሱ ነው ፆም ሲቀር፤ ፆም ለእኔ ነው። እኔ ምንዳውን እሰጣለሁ። የመልካም ስራዎች ምንዳ አስር እጥፍ ነው

ረመዷን ለአሏህ ብለን የምንሰራቸውን ስራዎች የምናድስበትና የበለጠ መልካም ስራዎችን ለመስራት እራሳችነን የምናነቃቃበት አመታዊ የስልጠና ፕሮግራም ነው። ፆም እራስን መቆጣጠር ያዳብራል። እንዲሁም እራስወዳድነትን ፣ ስግብግብነትን ፣ ስስታምነትን ፣ ስንፍናን እና ሌሎች ስህተቶቻችነን ሁሉ እንድንቀርፍ ይረዳናል። ይህ የትዕግስት ወር ርሃብ ወይም ችግር ምን ማለት እንደሆነ የምናውቅበት እድል ሲሆን ለድሆች ወይም ለምስኪኖች ያለንን አመለካከት በደግነት የተሞላ እንዲሆን ያደርጋል። እንዲሁም ፆም ለምቾትና ለድሎት ያለንን ውዴታ እንድንቆጣጠር ያስተምረናል።

ይሁንና እየፆምን በጣም ቢደክመን በደስታ መቋቋም ወይም መታገስ እንጅ ማማረር አይኖርብንም። እንዲሁ በተራዊህ ሶላት ወቅት ድካም ቢሰማን ይህንንም በፅናት ልንቋቋመው ይገባል።

እዚህ ላይ ልብ ልንለው (ልናስተውለው) የሚገባ ነገር ቢኖር የፆም አላማው ሰዎችን ማስቸገር ወይም በእነሱ ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ደግሞ የማይቋቋሙትን ሸክም መጫን ሳይሆን ለሃያሉ አሏህ ትዕዛዛት እምቢተኝነትን የምናሳይባቸው ወንጀሎች ወይም ፈተናዎች ከቁጥጥራችን ውጭ እንዳይሆኑ ወይም ደግሞ እኛ የሰው ልጆች የስሜታችን ባሪያ እንዳንሆን ወሰጢያን (መካከለኛነትን) እና መንፈሳዊ ስርአት የምንማርበት ፣ የአሏህን ረህማ በማግኘት ወደ ቀጥተኛው ጎዳና ዳግም የምንመለስበት ስለሆነ ነው። እውነተኛ

የአሏህ ባሪያ ለመሆን ባህሪያችን እና መንፈሳዊ ስርአታችን በሸሪአ ከተገለፀው ጋር ሊገጥም ይገባል። ሆኖም ፆም ለባህሪ ፣ ለስብዕናና ለመንፈሳዊ ስልጠና እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

በሙስሊም በተዘገበው ሐዲስ መሰረት ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) የረመዷን ወር በጀመረ ጊዜ የእዝነት በሮች (የጀነት በሮች) ይከፈታሉ። የጀሃሐነም በሮች ይቆለፋሉ፤ ሸይጧኖችም ይታሰራሉ ብለዋል።

عن أبي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُ يَقُولُ قَالَ رَسُولُ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ اللَّهُ عز وجل: «كُلُّ عَمَلِ ابْنِ آدَمَ لَهُ إِلَّا الصِّيَامَ فَإِنَّهُ لِي وَأَنَا أَجْزِي بِهِ وَالصِّيَامُ جُنَّةٌ وَإِذَا كَانَ يَوْمُ صَوْمِ أَحَدِكُمْ فَلَا يَرْفُثْ وَلَا يَصْخَبْ فَإِنْ سَابَّهُ أَحَدٌ أَوْ قَاتَلَهُ فَلْيَقُلْ إِنِّي امْرُؤٌ صَائِمٌ وَالَّذِي نَفْسُ مُحَمَّدٍ بِيَدِهِ لَخُلُوفُ فَمِ الصَّائِمِ أَطْيَبُ عِنْدَ اللَّهِ مِنْ رِيحِ الْمِسْكِ لِلصَّائِمِ فَرْحَتَانِ يَفْرَحُهُمَا إِذَا أَفْطَرَ فَرِحَ وَإِذَا لَقِيَ رَبَّهُ فَرِحَ بِصَوْمِهِ». متفق عليه

በቡኻሪ በተዘገበው ሐዲስ ደግሞ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ፆም ጋሻ ነው (ከሃራም ነገሮች፤ ከወንጀሎች መጠበቂያ ነው)። እናም ፆመኛ ሰው ከሚስቱ ጋር ያለውን የወሲብ ግንኙነት ፣ ንትርክንና ጭቅጭቅን ያስወግድ። የሆነ ሰው ቢጣላው ወይም ቢሰድበው ፆመኛ ነኝ ይበል። ነፍሴ በእጁ በሆነችው ይሁንብኝ ከአሏህ ዘንድ የሚፆም ሰው አፍ ሽታ ከሚስክ ሽታ በላይ የተወደደ ነው። የሚፆም ሰው ሁለት የደስታ ጊዜያቶች አሉት። አንደኛው ፆሙን በፈታ ጊዜ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጌታውን በሚገናኝ ጊዜ ነው። እናም በመፆሙ ምክኒያት ይደሰታል ብለዋል።

ሰዎች ከረመዷን ውጭ ባሉ ወራቶች የሚፈፅሟቸውን መጥፎ ነገሮች በዚህ ወር አመፀኛው ሸይጧን እንዳይቀሰቅስባቸው ተጠፍሮ



ይታሰራል። ታዲያ እዚህ ላይ ሸይጧን ተጠፍሮ ከታሰረ ለምን መጥፎ ነገሮች ወይም ወንጀሎች ይፈፀማሉ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። መልሱም መጥፎ ነገር በአመፀኛው ሸይጧን ምክኒያት ብቻ የሚፈጠር አይደለም። ሰዎች ለአስራ አንድ ወር ለሸይጧን ፣ ለስሜታቸው እና ለምኞታቸው ታዛዦች ሆነው ኑረዋል። ሆኖም ሸይጧን ቢታሰርም ፆመኛው ስሜቱንና መጥፎ ምኞቱን በኢማን በተቅዋ እስካለጎማቸው ድረስ መጥፎ ስራዎችን መስራቱ አይቀሬ ነው። ስለዚህ መጥፎ ነገር ሁሌም በረመዷን ውስጥም ሆነ ከረመዷን ውጭ ይፈፀማል።

ፆም ወደ አሏህ ፍራቻ የሚያደርስ መንገድ ነው። በቁርአን ውስጥ መፆም በእኛ ላይ የተደነገገው ተቅዋ (የአሏህ ፍራቻ) ይኖረን ዘንድ እንደሆነ ተገልፃል። በእርግጥ ይህ ተቅዋ በረመዷን ወቅት በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ ይጎለብታል። ዋናው ነገር ግን በዚህ ወር ያገኘነውን መንፈስና ትምህርት አመቱን ሙሉ እኛ ጋር እንዲቆይ ለማድረግ መጣር ነው። ሁላችነም ይህ ስሜት ወይም መንፈስ ከረመዷን ውጭ ባለው ህይወታችነም እኛ ጋር እንዲኖር መጣርና መታገል ይኖርብናል። በእርግጥም ትልቁ የረመዷን ግብና ፈተና ይህ ነው።

በሙስሊም በተዘገበው ሐዲስ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በአሏህ መንገድ ለሚፆም ማንኛውም የአሏህ ባሪያ በዚህ ቀን ምክኒያት አሏህ ፊቱን ሰባ አመት የሚያክል እርቀት ያህል ከጀሃነም እሳት ያርቅለታል ብለዋል።

ፆም የምግብና የደም ባንቧን ያጠባል። እነሱም የሸይጧን በዮች እንደሆኑ ይታወቃል። ይሁንና ፆም በጥጋበኝነት የሚፈፀም ወንጀልን ፣ ስጋዊ ስሜትንና ሃሳብን ፣ የእንቢተኝነትንና የትዕቢተኝነት ስሜት ያደክማል።

ፆም አካላዊ ጤናን ይጨምራል። ቆሻሻን ወይም የተመረዙ ነገሮችን ከአካላችን በማስወገድ ሆድን ያቀላል ፣ ደም ያጠራል ፣ የልብ አሰራርን የተስተካከለ ያደርጋል ፣ መንፈስን ያድሳል ፣ ስብዕናን ይቀርፃል። በፆምን ጊዜ ነፍሳችን የተነሳሳች ትሁት ትሆናለች፤ ስጋዊ ስሜታችነም ይወገዳል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ፆም ለአሏህ ትዕዛዝ ያለንን ታዛዥነት እና ባርነት የምናሳይበት እንደመሆኑ መጠን ትልቅ ምንዳ አለው።





# በሸዕባን ወር መፆም

የአካላችነን እና የመንፈሳችነን ጥንካሬ ጠብቀን ከዚህ ከተባረከ ወር እናተርፍ ዘንድ ከረመዷን በፊት አንድ ወይም ሁለት ቀን እንዳንፆም ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ነግረውናል።

በቡኻሪ በተዘገበው ሐዲስ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) አንዳችሁም ከረመዷን በፊት አንድ ወይም ሁለት ቀን መፆም አይኖርበትም። (ነዋፊል) ፆሙ ከቀኑ ጋር ከገጠመለት ያን ቀን መፆም ይችላል ብለዋል።

በሸዕባን ወር የቻልነውን ያክል ለመፆም መሞከር ይኖርብናል።

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከሱሃቦቻቸው አንዱን ሸዕባን መካከለኛው ላይ ትፆማለህን? ብለው ጠየቁት። ሶሃባውም አልፆምም ሲል መለሰላቸው። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ካልፆምክ ለሁለት ቀን ያህል ፁም ማለታቸው በሰሒህ ሙሊም ተዘግቧል።

የረመዷን ፆም እራስን ግልፅ ከሆነው ከአካላዊ ስሜት ፣ ከምግብ ፣ ከመጠጥ ፣ ከግብረስጋ ግኑኝነት መቆጠብ ብቻ ሳይሆን አካላችነን እና መንፈሳችነን ከመጥፎ ነገሮች ሁሉ መቆጠብ መቻል ነው። ህሊናችነን ከመጥፎ ሃሳቦች በመጠበቅ ፣ እጃችን የማይገባትን ወይም መጥፎ ነገር ባለመውሰድና ባለመንካት ፣ በአፍንጫችን ያልተፈቀዱ ነገሮችን ባለማሽተት ፣ በእግራችን ወንጀል የሚፈፀምባቸው ቦታዎች ባለመሄድ ፣ በአይናችን የተከለከሉ ነገሮችን ባለመመልከት ፣ በምላሳችን ውሸት

፣ ሃሜት ፣ ስድብ ከመናገር ፣ ነገር ከማዋሰድ ፣ ሌሎችን ከመዝለፍ ፣ ከመራገም ፣ ከመጥፎ ንግግር ፣ ከእንቶፈንቶ ወሬ ፣ በውሸት ነገር ላይ ተመርኩዞ ከመማል ልንቆጠብ ፣ በጆሯችን የአሉቧልታ ወይም የእንቶፈንቶ ወሬ ፣ ሙዚቃ ፣ የብልግና ንግግሮችን ባለማድመጥ ፣ ልባችነን ለዚች ብልጭልጭ ቀሳዊ አለም ያላትን ውዴታ በመግታትና በውስጧ ያሉ የሐሰት እምነቶችንና ፍልስፍናዎችን ውድቅ በድረግ ፣ ኒያችነን በማጥራት ሙሉ የአካል ክፍላችነን ልናፆማቸው ግድ ነው።

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በሐዲሳቸው መስሊም ብሎ ማለት ሙስሊሞችን በምላሱና በእጁ ከመጉዳት የራቀ ነው። ሙሐጅር (ስደተኛ) ብሎ ማለት ደግሞ አሏህ የከለከለውን ነገር ሁሉ የተወ(የተከለከለ) ነው ብለዋል።

በሌላ ሐዲስ ደግሞ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ትርፍ ንግግርና መጥፎ ስራን ያልተወ ሰው አሏህ ምግብና መጠጥ መተውን አይፈልግም ብለዋል።

በቡኻሪ በተዘገበው ሐዲስ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) አካል ውስጥ አንዷት ቁራጭ ስጋ አለች እሷ ከተስተካከለች ሙሉ አካል ይስተካከላል። ነገርግን እሷ ከተበላሸች ሙሉ አካል ይበላሻል። እሷም ልብ ናት ብለዋል።

ፆመኛ የሙዕሚን ልብ ከኩራት ፣ ከራስ ወዳድነት ፣ ከቅናት የተቆጠበች ናት። ምክኒያቱም ቅናት ፣ እራስወዳድነት ፣ ኩራት መልካም ስራን ያበላሻልና። አሏህ በቁርኑ ስለ ቅናት እንዲህ ይላል፡-

አሏህ ከችሮታው በሰጣቸው ነገር ላይ ይመቀኛሉን? {አል-ቁርአን 4:54}

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በሐዲሳቸው እሳት እንጨትን እንደሚበላው ሁሉ ቅናትም መልካም ስራን ይበላል ብለዋል።




# የፆም መንፈስን የሚቃረኑ ነገሮችን እናስወግድ

ብሉ ጠጡም፤ አታባክኑም። በእርግጥ! አሏህ አባካኞችን አይወድምና። {አል-ቁርአን 7:31}

አንዳንዶቻችን ለረመዷን የሚሆን ምግብ በያይነቱ በብዛት በማዘጋጀት ገንዘባችነን እናባክናለን። ያዘጋጀነውን ምግብ ሳንበላው ትንሽ በልተን የተረፈውን እንጥላለን። አባካኝነት በኢስላም የተጠላ ነው። አሏህ አባካኞችን አይወድም። እንዳይርበንን እና እንዳይጠማን ብለን ብዙ መመገብ የፆም አላማን ያጠፋብናል።

አብዘሃኛዎቻችን ደግሞ የፆም ጊዜያችንን በእንቅልፍ እናሳልፋለን። በዚህም ምክኒያት ያልፆምን ሀሉ ይመስለናል። ከመራብ ከመጠማት በተጨማሪ ኢባዳ ላይ የለንምና። ቀኑን በእንቅልፍ ሌሊቱን በእንቅልፍ የምናሳልፍ ከሆነ የፆም ትርጉሙ ምን ላይ ነው። ምናልባት ቀን የተወሰነ ተኝተን ሌሊት በኢባዳ እናሳልፋለን ልትሉ ትችላላችሁ። እስኪ ነፍስያችነን እንመርምር ምን ያህሎቻችነን ሌሊቱን በኢባዳ የምናሳልፍ? የመፆም ጥበቡ መራብ ፣ መጠማት ፣ ከሃራም ነገሮች ሁሉ መጠበቅና ቀንና ሌሊቱን በኢባዳ መትጋት መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

ፆም የሚያፈርሱና የማያፈርሱ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ፆምን የሚያፈርሱ የተለያዩ ነገሮች አሉ። ከነዚህም መካከል ግልፅ የሆኑት ወይም በግልፅ የተከለከሉት መብላት ፣ መጠጣት ፣ ግብረስጋ ግኑኝነት ማድረግ ፣ ከራስ ብልት ጋር መጫወት ናቸው። ነገርግን ረስተን ብንበላ ወይም ብንጠጣ ወይም ደግሞ በድንገት ቢያስታውከን ፆማችን አይፈርስም፤ ማካካስም አይጠበቅብንም። ይህን በተመለከተ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እየፆመ ያለ የሆነ ነገር ረስቶ የበላ ሰው ፆሙን ይሙላ (ይጨርስ)። እንዲበላና እንዲጠጣ ያደረገው አሏህ ነውና ብለዋል።

መድሃኒት መጠቀም በተመለከተ መድሃኒቱ በአፍ ወይም በአፍንጫ የማይወሰድና ምግብ እስካልሆነ ድረስ ከመጠቀም የሚያግደን ወይም የሚከለለልን ነገር የለም።



# በረመዷን ወቅት ቁርአን መቅራት

﴿شَهۡرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلۡقُرۡءَانُ هُدٗى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَٰتٖ مِّنَ ٱلۡهُدَىٰ
وَٱلۡفُرۡقَانِۚ فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهۡرَ فَلۡيَصُمۡهُۖ وَمَن كَانَ مَرِيضًا أَوۡ عَلَىٰ سَفَرٖ فَعِدَّةٞ
مِّنۡ أَيَّامٍ أُخَرَۗ يُرِيدُ ٱللَّهُ بِكُمُ ٱلۡيُسۡرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ ٱلۡعُسۡرَ وَلِتُكۡمِلُواْ ٱلۡعِدَّةَ
وَلِتُكَبِّرُواْ ٱللَّهَ عَلَىٰ مَا هَدَىٰكُمۡ وَلَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ﴾ [البقرة: ١٨٥]

ረመዷን ቁርአን ለሰው ልጆች እንደ መመሪያ፤ (በእውነትና በውሸት መካከል) መለያ እና ግልፅ መመሪያና ማስረጃ ሆኖ የወረደበት ወር ነው። {አል-ቁርአን 2:185}

ሙሉ የረመዷን ወር ከሌሎች ኢባዳዎች ጋር ቁርአን በመቅራት ልናሳልፈው ይገባል። አሏህ በሱረቱ ሉቅማን አንቀፅ 3 ላይ እንደገለፀው ቁርአን “ለመልካም ሰሪዎች መመሪያና እዝነት ነው።” ቁርአን ህይወት ፣ ሽፈእ ፣ ደስታ ፣ ምንዳ ፣ እዝነት ፣ መድሃኒት ፣ መለኮዊ አስተምህሮት ፣ ከህግም በላይ ህግ የሆነ ዘላለማዊ ጥበብ ነው።

በቡኻሪ በተዘገበ ሐዲስ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ቁርአን አንብቡ በእርግጥ በፍርዱ ቀን ሽፈአ(አማላጅ) ይሆንላችኋልና ብለዋል።

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በመጨረሻ አመታቸው ረመዷን ውስጥ ሁለት ጊዜ አክትመዋል። እኛ ሙስሊሞችም የረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ፈለግ በመከተል በረመዷን ወቅት ቢያንስ አንድ ጊዜ ማኽተም ይኖርብናል።

ይሁንእንጅ በአሁኑ ወቅት አብዛሃኛዎቻችን ቁርአን የምንቀራው በረመዷን ብቻ እየሆነ ነው። ይባስ ብሎ ለማከተም የሚደረግው ጥረት የተራዊህ ወይም የተሃጁድ ሶላት ላይ ነው። በተራዊህ ሶላት ለማኽተም ሩጫ ነው። በእርግጥ ይህ ተግባር የቁርአን አስተህሮትን ይቃረናል። ምክኒያቱም አሏሁ አዘወጀል "ቁርአንን በዝግታ አንብብ" ብሏል (73:4)። ኢብን ከሲር ይህን የቁአን አንቀፅ ሲያብራሩ ይህ ማለት ቁርአንን ለመረዳትና ለማስተንተን ይረዳህ ዘንድ ቀስ ብለህ ቅራ ማለት ነው። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ይቀሩ የነበረውም እንዲህ ነው ሲሉ አብራርተዋል። ሆኖም ቁርአን ስንቀራ ወይም በረመዷን ለማኽተም ስንጥር ይህን የቁርአን አያ ተከትለን መሆን ይኖርበታል። የበለጠ ወደ አሏህ ለመቅረብ ስንቀራ እያስተነተን እና ተረድተነው ይሁን። ቁርአን ማንበብ የማንችል ሰዎች እያንዳንዷን ቀን በሲዲ የተቀረፀ ቁርአን ለማዳመጥ እንሞክር። ወይም ደግሞ በአፍ መፍቻ ቋንቋችን የተተረጎመ ቁርአን በማንበብ ማሳለፍ ይኖርብናል።




# የተራዊህ ሶላት

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በቅን እምነትና ከአሏህ ምንዳ እንደሚያገኝበት አስቦ በቀደር ምሽት ሶላቶችን የሰገደ ያለፉ ወንጀሎቹ ሁሉ ይማሩለታል ብለዋል።

በዚህ ወር ተራዊህን ለመስገድ በተለይ ደግሞ በጀመአ ለመስገድ ትልቅ ጥረት ማድረግ አለብን። ምክኒያቱም የተራዊህ ሶላት ከሌሎቹ ምሽቶች የበለጠ ልዩ ምንዳ አለውና። ተራዊህ የአካላዊና የመንፈሳዊ ስልጠና አካል ነው።

አኢሻ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፈችው ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) አንድ ምሽት መስጊድ ውስጥ ሰገዱ፤ ሰዎችም ከሳቸው ጋር ሰገዱ በቀጣዩ ምሽትም ሰገዱ፤ ብዙ ሰዎችም ነበሩ። ከዚያ በሶስተኛው ወይም በአራተኛው ምሽት (ብዙ ሰዎች) ተሰባሰቡ። ነገርግን ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) (የተራዊህ) ሶላቱን ለመምራት አልመጡላቸውም ነበር። ጠዋት ላይ እንዲህ አሉ "ስትሰሩ የነበረውን ነገር አይቻለሁ። ነገርግን ይህ ሶላት በእናንተ ላይ ግዴታ እንዳይሆንባችሁ ፈርቼ ወደ እናንተ መምጣት (ሶላት መምራቱን) ተውኩ" ብለዋል።

# ልግስና በረመዷን

በቡኻሪ እንደተዘገበው ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በተፈጥሮ በጣም ለጋስ (ቸር) ሰው ነበሩ። በረመዷን ወር ከሌላው ጊዜ ይበልጥ በጣም ላጋስ ይሆኑ ነበር።

አሏህ(ሱ.ወ.ተ) ከሰጠን ነገር በረመዷን ውስጥ ሶደቃም ይሁን ዘካ ለመስጠት መሞከር ይኖርብናል። ማጣት አያሳስበን በማንኛውም ጊዜ የሆነ ነገር ስንሰጥ አሏሁ አዘወጀል አካላዊ ፣ መንፈሳዊ ፣ ህሊናዊ ሁኔታችንን ያቀልልናል፤ ሲሳያችነንም ያሰፋልናል። ሶደቃ ግዴታ ገንዘብ ብቻ አይደለም፤ መልካም ስራም ይሆናል። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) መልካም ንግግር ሶደቃ ነው። መጥፎ ነገር ከመንገድ ማስወገድ ሶደቃ ነው አይደል ያሉት። ይሁን እንጅ ገንዘብ ካለን የተወሰነ ለሚገባቸው ሰዎች መስጠት ይኖርብናል። ብዙ ሙስሊሞችም ዘካቸውን በረመዷን ውስጥ ይከፍላሉ። ምክኒያቱም ምንዳው በረመዷን ውስጥ በላጭ ነውና። ሐብት ልክ እንደ ውሃ ነው። ፍሰቱን ከገደብነው ጨውጨው የሚልና የተበከለ ይሆናል። ፍሰቱን ሲቀጥል ግን ንፁህና ጣፋጭ ይሆናል።

በትርሚዘ በተዘገበው ሐዲስ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ይህ የአማኞች ሲሳይ የሚጨምርበት የልግስና ወር ነው። ፆመኛን የመገበ ወይም (የሚያፈጥርበትን) አንዲት ተምር ወይም አንድ ጉንጭ ውሃ የሰጠ

ሰው ለወንጀሎቹ መሃርታ ያገኛል፤ ከጀሃነም እሳት ይድናል። እሱም ተመሳሳይ ምንዳ ያገኛል ብለዋል።

ፆመኛን ማስፈጠር ትልቅ ምንዳ ያለው በመሆኑ ምክኒያት በብዙ ቦታዎች ማፍጠሪያ መስጊድ ውስጥ ይቀርባል። ወይም ደግሞ ሰዎችን ከቤታቸው ጠርተው ያስፈጥራሉ። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ከሌሎች ሙስሊም እትህ ወንድሞቻቸው ጋር የሚጋሩትን ነገር ይዘው ወደ መስጊድ ይሄዳሉ። ይህ ግንኙነት በኡማችን መካከል ትክክለኛ ወንድማማችነትን ለመፍጠር ይረዳናል። ሆኖም ይህ አይነት ተግ ዘለቄታ ሊኖረው ይገባል።

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) አንድ ሰው በሞተ ጊዜ ሁሉም ስራዎቹ ይቋረጣሉ ሶስት ስራዎቹ ሲቀሩ። ቀጣይነት ያለው ሶደቃ ፣ ከእሱ (ሰዎች) የተጠቀሙበት እውቀትና ለእነሱ የሚፀልይላቸው ሷሊህ ልጅ ናቸው ብለዋል።



# የረመዷን ወር የሚጀምረው እንዴት ነው?

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) አዲሷን ጨረቃ እስክታዩ ድረስ አትፁሙ፤ አታፍጥሩም እስክታዩት ድረስ። ነገርግን የአየር ንብረቱ ደመናማ ከሆነ (ሰአቱን) አስሉት ብለዋል።

ይህ ታላቅ ወር በኢስላም የቀን አቆጣጠር መሠረት በትክክል መጀመር ይኖርብናል። በቁርአንና በሱና ጨረቃን ተመልክተን መፆም እንዳለብን ተገልፃል። ጨረቃ ከታየች ወሩ መጀመሩ ግልፅ ይሆናል።

# የረመዷን ደንቦች

በአቡዳውድ በተዘገበው ሐዲስ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከንጋት በፊት ለመፆም ያልወሰነ (ያልነያ_ያላሰበ) አልፆመም ብለዋል።

ለሱሑር ለመነሳት የቻልነውን ይህል መሞከር አለብን። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከንጋት በፊት ጥቂት ብሉ በዚያን ጊዜ ምግብ መብላቱ በረካ አለውና ብለዋል።

ብዙዎቻችን በራሳችን ደካማነት ምክኒያት ይህን ትልቅ በረካ እናጣለን። ምግብ ባይኖር እንኳ አንድ ተምርና ውሃ መውሰድ ይኖርብናል። ከንጋት በፊት ያለው ጊዜ እንደ በርካ የሚታሰብበት ምክኒያት የሌሊቱ አንድ ሶስተኛ በመሆኑ ፣ አምላክ ወደ ታችኛው ሰማይ የሚወርድበትና ምህረቱን የሚቸርበት ጊዜ ስለሆነ ነው። ሌላው ዱአ ተቀባይነት የሚያገኝበት ልዩ ጊዜ በመሆኑ ነው።

ሱሑር ከበላን ቡኋላና ከፈጅር ሶላት በፊት የተወሰነ ትርፍ ጊዜ ሊኖረን ይገባል።

አነስ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፈው ዘይድ ቢን ሳቢጥ ከነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ጋር ሱሑር በላን። እናም (ነብዩ) ለሶላት ቆሙ። በሱሑርና በአዛን መካከል ያለው ትርፍ ጊዜ ምን ያህል ነው ስል ጠየኳቸው። በሱሑርና በአዛን

መካከል ያለው ትርፍ ጊዜ 50 የቁርአን አያዎችን ለመቅራት በቂ የሆነ ነው ሲሉ መልሰዋል ብሏል።

ለማፍጠር መጣደፍ ወይም መፍጠን ይኖርብናል። ነብዩ(ሠ.ዐ.ወ) ሰዎች በቀጥተኛው መንገድ ላይ ሆነው ይቆያሉ ለማፍጠር እስከተጣደፉ ድረስ ብለዋልና።

በተምር እና በውሃ ማፍጠር ሱና ነው።

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) አንዳችሁ በፆማችሁ ጊዜ ፆሙን በተምር ይፍታ። ምንም ካላገኘ በውሃ ያፍጥር ብለዋል።

ሲዋክ (መፋቂያ) መጠቀም ሱና ነው። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እየፆሙ ሲዋክ ይጠቀሙ ነበር። ሲዋክ በመጠቀም የአፋችንን ፣ የጥርሳችንን ፣ የድዳችንን ንፅህና ሁሌም መጠበቅ ይኖርብናል በተለይ በፆም ወቅት።





# የፆመኛ ሰው ዱአ

የፆመኛ ሰው ዱአ በፍፁም ምላሽ የማያጣ ነው። ነብያችን(ሰ.ዐ.ወ) በሐዲሳቸው ፆመኛ ሙስሊም ከአሏህ ለለመነው ማንኛውም ነገር ከሚከተሉት ሶስት ነገሮች አንዱን ይቀበላል (ያገኛል)። የጠየቀውን ነገር በቀጥታ ያገኛል ወይም ባሰበው ነገር ፈንታ አሏህ ከመንገዱ መጥፎ ነገር ያስወግድለታል ወይም ደግሞ ለለመነው ነገር ምንዳ ለመጭው አለም ይቀመጥለታል ብለዋል።

ስለዚህ ያለ መሰልቸት ዱአ ማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው። እሱን በማንኛውም ጊዜ ችላ ማለት ደግሞ ትልቅ እጦት ነው። አሏህ ለኛ ደህንነትና ጥቅም የሚሆነን ነገር ይሰጠናል። ዱአችን ተቀባይነት ባያገኝ እንኳ መለስ ብለን እራሳችንን ልንመረምርና ዱአችን ተቀባይነት የሚያገኝባቸውን ሁኔታዎች ልናጤን ይገባል። በሐራም ምግብ ፆሙን የሚፈታ ሰው ልክ መድሃኒትና መርዝ ቀላቅሎ እንደሚወስድ በሽተኛ ሰው ነው።

# የአላህን መሃርታ መለመን

የአሏህን መሃርታ ከምንሻባቸው ነገሮች አንዱ  አሏህ ያዘዘንን ነገር መታዘዝና ከከለከለን ነገር ሁሉ መራቅ ነው። ለምሳሌ ፆማችነን በትክክል በመፆም ፣ ሶላታችነን በወቅቱ በመስገድ ፣ የተራዊህ ሶላት በመስገድ ፣ ላለፉት ወንጀሎቻችን ተውባ በማድረግ ነው። ቅን የሆኑ ሰዎች ከትልልቅ ወንጀሎች ከራቁ አመቱን ሙሉ የሰሯቸው ትንንሽ ወንጀሎች በረመዷን እንደሚማርላቸው ያውቃሉ። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) የረመዷን የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት አሏህ በሙዕሚኖች ላይ እዝነቱን የሚያዘንብበት የእዝነት ጊዜ ነው። ቀጣዮቹ አስር የረመዷን ቀናት ደግሞ ሙዕሚኖች በመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በመፆማቸው ምህረት የሚያገኙበት ነው። የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ደግሞ ከጀሃነም እሳት የሚጠበቁበት (አሏህ ሰዎችን ከጀሃነም እሳት የሚያወጣበት) ነው ብለዋል። ታዲያ ይህን ወር በኢባዳ ፣ በዱአ ፣ በዚክር ፣ በስቲግፋር  ማሳለፍ ይኖርብናል። ብዙ እስቲግፋር የምናደርግ ከሆነ አሏህ ከችግሮቻችን ሁሉ የምንወጣበትን በር ይከፍትልናል። እንዲሁም ከጭንቀታችን ያላቅቀናል።

# ለይለቱል ቀድር

አሏህ በቁርአኑ በሱረቱል ቀደር ላይ እንዲህ ብሏል፡-

﴿إِنَّآ أَنزَلۡنَٰهُ فِي لَيۡلَةِ ٱلۡقَدۡرِ﴾ [القدر: ١]

እኛ (ቁርኣኑን) በመወሰኛይቱ ሌሊት አወረድነው፡

﴿وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا لَيۡلَةُ ٱلۡقَدۡرِ﴾ [القدر: ٢]

መወሰኛይቱም ሌሊተ ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ?

﴿لَيۡلَةُ ٱلۡقَدۡرِ خَيۡرٞ مِّنۡ أَلۡفِ شَهۡرٖ﴾ [القدر: ٣]

መወሰኛይቱ ሌሊት ከሺሕ ወር በላጭ ናት፡፡

﴿تَنَزَّلُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ وَٱلرُّوحُ فِيهَا بِإِذۡنِ رَبِّهِم مِّن كُلِّ أَمۡرٖ﴾ [القدر: ٤]

በርሷ ውስጥ መላእክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ይወርዳሉ፡፡

﴿سَلَٰمٌ هِيَ حَتَّىٰ مَطۡلَعِ ٱلۡفَجۡرِ﴾ [القدر: ٥]

እርስዋ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሰላም ብቻ ናት፡

በዚህ አያ ለይለቱል ቀድር ከሺ ወራቶች በላይ በላጭ እንደሆነች ተገልፃል። ታዲያ ማነው ከእኛ መካከል ይችን ሌሊት በኢባዳ በማሳለፍ የዚችን ሌሊት ሙሉ በረካዋን ለማግኘት የሚተጋ?

በሰኺህ ሙስሊም በተዘገበው ሐዲስ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በመጨረሻዎቹ አስር ሌሊቶች ለይለቱል ቀድርን ሻቱ (ፈልጉ) ብለዋል።

በመጨረሻዎቹ የረመዷን ምሽቶች አብዝተን ቁርአን መቅራት ፣ አሏህን ማውሳት እና ዱአ ማብዛት ይኖርብናል። ምክኒያቱም የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ሶደቃ ወይም ዘካ የምንሰጥበት ፣ ነፍስያችንን የምንመረምርበት ፣ ዱአ አብዝተን የምናደርግበት ፣ መሃርታን የምንለምንበት ፣ ፆማችንን ሙሉ የምናደርግበት ጊዜ ነውና።

በመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ጥረታችንን ወይም ኢባዳችንን እጥፍ እናደርግ ዘንድ አሏህ(ሱ.ወ.ተ) የለይለቱል ቀድር ቀን መቼ እንደሆነ ደብቆታል።

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በለይለቱል ቀድር አምኖበትና ከአሏህ ምንዳ እንደሚያገኝ ተስፋ አድርጎ ለሶላት የቆመ ሰው ያለፉት ወንጀሎቹ ሁሉ ይማሩለታል ብለዋል።

በሰኺህ ሙስሊም በተዘገበው ሐዲስ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሌላው ጊዜ በበለጠ በመጨረሻዎቹ አስር ሌሊት በኢባዳ ላይ ይተጉ ነበር።

በዚህ ጊዜ ከሰዎች ጋር ያላቸውን ግኑኝነት በመገደብ ዱአቸውን ያጧጡፉ ነበር። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ይህን ያደርጉ የነበረው ልባቸው የበለጠ አሏህ ጋር እንዲሆንና ህሊናቸውን ከአለማዊ ጉዳይ ለማላቀቅ ነበር።

በቡኻሪ በተዘገበው ሐዲስ የረመዷን የመጨረሻዎቹን አስር ቀናት መጀመሩን ተከትሎ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ጠንክረው ይሰራሉ፤ ሌሊቱን



ሙሉ ሶላት ይሰግዳሉ። ቤተሰባቸውንም ለሶላት ይቀሰቅሱ ነበር።

ዘካቱል ፊጥር ምንድነው?

ዘካቱል ፊጥር ማንኛውም መክፈል የሚችል ሙስሊም በእራሱና በእያንድንዱ የቤተሰቡ አባል ስም በተናጠል ከረመዷን መጨረሻ ላይ ከኢድ ሶላት በፊት ሊከፍለው የሚገባ ግዴታ የሆነ የድሆች መዋጮ ምፅዋት ነው።

የዘካቱል ፊጥር አከፋፈል ሁኔታ

የዘካቱል ፊጥር ክፍያ መሰረታዊ ፍላጎቱን ከሚያሟላበት በላይ የሆነ ሶስት ኪሎግራም ተምር ወይም ገብስ ወይም ደግሞ ተመሳሳይ የምግብ እህሎች ባሉት ማንኛውም ሙስሊም ላይ ግዴታ ሲሆን መክፈል የሚችል ሰው በእራሱና ቤተሰብ የመያስተዳድር ከሆነ በእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ስም በተናጠል መክፈል ይኖርበታል። ነገርግን ከቤተሰቡ አባል ውስጥ በራሱ መክፈል የሚችል ሰው ካለ በእራሱ ስም መክፈሉ በላጭ ነው። ከእናቱ ማህፀን ውስጥ ባለ ልጅ ስም ሊከፍል ይችላል ነገርግን ግዴታ አይደለም። ኡስማን ኢብን አፋን(ረ.ዐ) ማህፀን ውስጥ ባለው ልጁ ስም ዘካቱል ፊጥር ይከፍል ነበር።

ስለዚህ የዘካቱል ፊጥር ክፍያ መጠን ሶስት ኪሎ የሆነ ገብስ ፣ በቆሎ ፣ ሩዝ ፣ ወይም ደግሞ ሌላ የምግብ አይነት ሊሆን ይችላል። ነገርግን ምግብ ያልሆነ ልክ እንደ ልብስ ወይም የቤት እቃ ያሉ ነገሮችን መክፈል አይቻልም።

ለማነው የሚሰጠው?

ዘካው ሊከፋፈል የሚገባው ዘካው በተከፈለበት ሐገር ውስጥ

ለሚኖሩ ችግረኞችና ድሆች ነው። ሆኖም ግን ከፋዩ ካለበት ቦታ ችግረኞችን ወይም ድሆችን ካላወቀ ሌላ ቦታ ላሉ ችግረኞች ወይም ድሆች መክፈል ይችላል።

የሚከፈልበት ጊዜ

ዘካቱል ፊጥር የሚከፈልበት ጊዜ ከኢድ ቀን ቀደም ብሎ ሲሆን የኢድ ቀን ሶላቱ ከመሰገዱ በፊት ጧት ላይ መክፈሉ ተመራጭ ነው። ይሁን እንጅ ከኢድ በፊት አንድ ወይም ሁለት ቀን ቀደም ብሎ መክፈል ይፈቀዳል።

የዘካቱል ፊጥር ክፍያ ያለምንም ተጨባጭ ምክኒያት ከኢድ ሶላት ብኋላ ለመክፈል ማዘግየት አይፈቀድም። የኢድን ዜና ዘግይቶ ካወቀ ወይም ዘካቱል ፊጥር ማንም የማይቀበልበት ቦታ ከሆነ ያለው ብኋላ ላይ ሊከፍለው ይችላል። ያለምንም ተጨባጭ ምክኒያት ክፍያውን ያዘገየ ግን ክፍያው እንደ ዘካቱል ፊጥር ሳይሆን የሚቆጠርለት እንደ ሶደቃ ነው የሚታሰበው። ዘካውን መክፈል ይኖርበታል ነገርግን የዘካቱል ፊጥርን ልዩ ምንዳ አያገኝም።

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከሶላት (ከኢድ ሶላት) በፊት ዘካ የከፈለ ሰው ተቀባይነት እንዳገኘ ዘካ ይቆጠርለታል። ከሶላት (ከኢድ ሶላት) ብኋላ የከፈለ ሰው እንደ ሶደቃ ይቆጠራለታል ብለዋል። ይህ ሐዲስ በአቡዳውድ ፣ በነሳኢና በኢብን ማጃ ተዘግቧል።

ዘካቱል ፊጥርን የተመለከቱ ውሳኔዎች(ደንቦች)

የአንድን ሰው ዘካቱል ፊጥር ክፍያ ለተወሰኑ ድሆች ማከፋፈል ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን የዘካቱል ፊጥር ክፍያ ለአንድ ሰው





መስጠት ይፈቀዳል። እዲሁም የዘካቱል ፊጥር ክፍያን አንድ እቃ ላይ ሰብስቦ ሳይለኩ ለድሆች ማከፋፈል ይችላሉ።

መጥፎ ነገሮችን በዘካቱል ፊጥር መልክ መክፈል አይፈቀድም። አሏህ እንዲህ ይላል፦

﴿يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَنفِقُواْ مِن طَيِّبَٰتِ مَا كَسَبۡتُمۡ وَمِمَّآ أَخۡرَجۡنَا لَكُم مِّنَ ٱلۡأَرۡضِۖ وَلَا تَيَمَّمُواْ ٱلۡخَبِيثَ مِنۡهُ تُنفِقُونَ وَلَسۡتُم بِـَٔاخِذِيهِ إِلَّآ أَن تُغۡمِضُواْ فِيهِۚ وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ غَنِيٌّ حَمِيدٌ﴾ [البقرة: ٢٦٧]

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ካፈራችሁትና ከዚያም ለእናንተ ከምድር ካወጣንላችሁ ከመልካሙ ለግሱ፡፡ መጥፎውንም (ለመስጠት) አታስቡ፡፡ በእርሱ ዓይኖቻችሁን ጨፍናችሁ እንጂ የማትወስዱት ስትኾኑ ከእርሱ (ከመጥፎው) ትሰጣላችሁን አላህም ተብቃቂ ምስጉን መኾኑን ዕወቁ፡፡



IslamHouse.com

IslamHouseAM/ Bengali.IslamHouse islamhouse.com/am/

channel/UC0T_q-4JkqIMTfmxa1L3kTw

For more details visit
www.GuideToIslam.com

GUIDE TO ISLAM

contact us :Books@guidetoislam.com

Guidetolslam.org Guidetoislam1 Guidetoislam www.Guidetoislam.com

المكتب التعاوني للدعوة وتوعية الجاليات بالربوة
هاتف: ٩٦٦١١٤٤٥٤٩٠٠+ فاكس: ٩٦٦١١٤٩٧٠١٢٦+ ص ب: ٢٩٤٦٥ الرياض: ١١٤٥٧
ISLAMIC PROPAGATION OFFICE IN RABWAH
P.O.BOX 29465 RIYADH 11457 TEL: +966 11 4454900 FAX: +966 11 4970126